በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ቤተ ክርስቲያን - ክፍል 4


## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com


*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ኅዳር ፲፯ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.

# <u>ቤተ ክርስቲያን - በዘመነ ሐዋርያት</u>

- "ወዲያውም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ በምኵራቦቹ ሰበከ።" *<u>የሐዋ. ሥራ. 9፡20።</u>*

*<u>መግቢያ</u>*

- ሐዋርያት ጌታችን ያደርጉ ዘንድ እንዳዘዛቸው አድርገው ሁሉን አከናውነዋል። “እንዲህም አላቸው፦ ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ።” *<u>ማር 16፡15።</u>*
- ልበ አምላክ ዳዊት የተናገረው ትንቢትም ተፈጽሞለታል። “ድምፃቸው ወደ ምድር ሁሉ፥ ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ ወጣ።” *<u>መዝ 19፡4።</u>*
- ክርስትና ለዓለም የተስፋፋበትን ሁኔታ ለመረዳት ሐዋርያቱን በሚከተለው መንገድ በመክፈል ልንረዳ እንችላለን።

*<u>ምድብ አንድ</u>*

- ቅዱስ ጴጥሮስ፣ ቅዱስ እንድርያስ፣ ቅዱስ ማቴዎስንና ቅዱስ በርተሎሜዎስን ያካተተ ነበር።

*<u>ቅዱስ ጴጥሮስ፦</u>* መልእክቱን በጻፈላቸው ሥፍራዎች አስተምሯል። “የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ጴጥሮስ፥ እግዚአብሔር አብ አስቀድሞ እንዳወቃቸው በመንፈስም እንደሚቀደሱ፥ ይታዘዙና በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይረጩ ዘንድ ለተመረጡት በጳንጦስና በገላትያ በቀጳዶቅያም በእስያም በቢታንያም ለተበተኑ መጻተኞች፤ ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ።” *<u>ቀዳ ጴጥ 1፡1።</u>*

*<u>ቅዱስ እንድርያስ፦</u>* በስኪታ (የሩሲያ አካል በሆነችው ግዛት)፣ የቦስፎራን ግዛት በሆነችው በጥቁር ባሕር በስተምሥራቅ በሲኖጴ እንዲሁም በጥቁር ባሕር በስተምስራቅ አስተምሯል።

*<u>ቅዱስ ማቴዎስ፦</u>* በፐርሺያ ባሕረ ሰላጤ አስተምሮ በዚያው በሰማዕትነት አርፏል። ከእንድርያስም ጋር በቦስፎራን ግዛት ከቅዱስ እንድርያስ ጋርም አስተምሯል።

*<u>ቅዱስ በርተሎሜዎስ፦</u>* በሕንድ የሕንድ ሰዎች መምህራቸው እንደሆነ እስኪረዱ ድረስ አስተምሯል። ከቅዱስ ማቴዎስና ከቅዱስ እንድርያስም ጋር በቦስፎራን ግዛትም አስተምሯል።

# ቤተ ክርስቲያን - በዘመነ ሐዋርያት

***ምድብ ሁለት:-***

- ቅዱስ ቶማስ፣ ቅዱስ ታዴዎስንና፣ ቅዱስ ስምዖንን ያካተተ ነበር፡፡ እነዚህም የመጀመሪያዎቹ ምደቦች ባስተማሩበት ምሥራቃዊ አቅጣጫ አስተምረዋል፡፡

***ቅዱስ ቶማስ:-*** በኤዴሳና በሕንድ አስተምሯል፡፡

***ቅዱስ ታዴዎስ:-*** ለአምስት ዓመታት ያህል አይሁድ በብዛት ይኖሩ በነበረበት በሁለቱ ወንዞች መካከልና እንዲሁም በኤዴሳ አስተምሯል፡፡

***ቅዱስ ስምዖን:-*** በባብልና በሶርያ አስተምሯል፡፡

***ምድብ ሦስት:-***

***ቅዱስ ዮሐንስና ቅዱስ ፊሊጶስ:-*** በታናሽ እስያ አስተምረዋል፡፡

***ቅዱስ ዮሐንስ:-*** በኤፌሶን አስተምሯል፡፡

***ቅዱስ ፊሊጶስ:-*** በፈርጊያና በሄራቦሊስ አስተምሯል፡፡

***ቅዱስ ጳውሎስ:-*** ከሐዋርያቱ ሁሉ ይልቅ አስተምሯል፡፡ ***ቀዳ ቆሮ 15:10፣ ካል ቆሮ 11:23፡፡*** በደማስቆ፣ በሶርያ፣ በጠርሴስ፣ በአንጣኪያ፣ በሳይፕረስ፣ በታናሽ እስያ፣ በፔሲዲያ፣ በደርቤን፣ በልስጥራ፣ በገላትያ፣ በቴፌሶንና በግሪክ በሚገኙ ከተሞች አስተምሯል፡፡

# ለጥንታዊው ዓለም ክርስትና እንዲስፋፋ የረዱ ምክንያቶች

- ያለጥርጥር ዋናው ምክንያት የክርስትና ሃይማኖት አምላካዊ ወይም መለኮታዊ ሃይማኖት በመሆኑ የመለኮት ፈቃድና ረዳትነት ያለው መሆኑ ሲሆን ክርስትና በጊዜው የነበሩ ሌሎች ሃይማኖቶችን አሸንፎ እንዲስፋፋ የረዱት ሌሎች ነባራዊ ሁኔታዎችም ነበሩ፡፡ እነዚህም፡-
  1. የአይሁድ መበተን
     አይሁድ በመላው የሮማ ግዛት ተበትነው የነበሩ ሲሆን በሚኖሩባቸውም ከተሞች ምኩራቦች ነበሯቸው፡፡ የአይሁድ ምኩራቦችም ክርስትናን በየከተማው ለመስበክ የጠቀሙ ዋናዎቹ ማዕከላት ናቸው፡፡
  2. የሮማ መንግሥት ጥንካሬና በዓለምም ላይ የነበረው ተጽእኖ፣ እንዲሁም በበርካታ አገሮች የነበረው የተረጋጋ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሕይወት
  3. የበርካታ መንገዶች መኖርና፣ በባሕርም ለመጓጓዝ የሚያስችሉ መሠረታዊ ቁሳቁሶችና መንገዶች መኖር
  4. የማስተማሪያ ቦታዎች
     - ሐዋርያት በአይሁድ ምኩራብ አስተምረዋል፡፡ “ወዲያውም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ በምኵራቦቹ ሰበከ፡፡” ሥራ 9፡20፡፡
     - በየቤቶቹ እየሄዱም አስተምረዋል፡፡ “ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ንስሐንና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመንን ለአይሁድና ለግሪክ ሰዎች እየመሰከርሁ በጉባኤም በየቤታችሁም አወራሁላችሁና አስተማርኋችሁ እንጂ፥ ከሚጠቅማችሁ ነገር አንዳች ስንኳ አላስቀረሁባችሁም፡፡” ሥራ 20፡20፡፡
     - በኤፌሶን በትምህርት ቤት አስተምረዋል፡፡ “አንዳንዶች ግን እልከኞች ሆነው በሕዝብ ፊት መንገዱን እየሰደቡ ባላመኑ ጊዜ፥ ከእነርሱ ርቆ ደቀ መዛሙርትን ለየ፥ ጢራኖስም በሚሉት በትምህርት ቤት ዕለት ዕለት ይነጋገር ነበር፡፡” ሥራ 19፡9፡፡
     - በገዢዎችም ቤት አስተምረዋል፡፡ “እርሱም አስተዋይ ሰው ከሆነው ሰርግዮስ ጳውሎስ ከሚባለው አገረ ገዥ ጋር ነበረ፡፡ ይህም በርናባስንና ሳውልን ወደ እርሱ ጠርቶ የእግዚአብሔርን ቃል ሊሰማ ፈለገ፡፡” ሥራ 13፡7፡፡
     - በገበያም አስተምረዋል፡፡ “ስለዚህም በምኵራብ ከአይሁድና እግዚአብሔርን ከሚያመልኩ ሰዎች ጋር በየቀኑም በገበያ ከሚያገኛቸው ጋር ይነጋገር ነበር፡፡ ከኤፊቆሮስ ወገንና ኢስጦኢኮችም ከተባሉት ፈላስፎች አንዳንዶቹ ከእርሱ ጋር ተገናኙ፡፡ አንዳንዶቹም፡፡ ይህ ለፍላፊ ምን ሊናገር ይወዳል? አሉ፤ ሌሎችም የኢየሱስንና የትንሣኤውን ወንጌል ስለ ሰበከላቸው፡፡ አዲሶችን አማልክት የሚያወራ ይመስላል አሉ፡፡ ይዘውም፡፡ ይህ የምትናገረው አዲስ ትምህርት ምን እንደሆነ እናውቅ ዘንድ ይቻለናልን? በጆሮአችን እንግዳ ነገር ታሰማናለህና፤ እንግዲህ ይህ ነገር ምን እንደሆነ እናውቅ ዘንድ እንፈቅዳለን ብለው አርዮስፋጎስ ወደ ተባለው ስፍራ ወሰዱት፡፡” ሥራ 17፡17-19፡፡
     - ቅ. ጳውሎስ በውሃ ዳርቻዎችም አስተምሯል፡፡ “በሰንበት ቀንም ከከተማው በር ውጭ የጸሎት ስፍራ በዚያ መሆኑን ስላሰብን ወደ ወንዝ አጠገብ ወጣን፤ ተቀምጠንም ለተሰበሰቡት ሴቶች ተናገርን፡፡” ሥራ 16፡13፡፡
     - የማስተማሪያ ጊዜያት፡- በቀንም ሆነ በማታ ያስተምሩ ነበር፡፡ “ስለዚህ ሦስት ዓመት ሌሊትና ቀን በእንባ እያንዳንዳችሁን ከመገሠጽ እንዳላቋረጥሁ እያሰባችሁ ትጉ፡፡” ሥራ 20፡31፡፡

# በሐዋርያዊቱ ቤተ ክርስቲያንና በመንግሥት መካከል የነበረው ግኑኙነት

- ሮማውያን አስቀድመው ክርስትናን ከአይሁድ ሃይማኖት የወጣ ሃይማኖት አድርገው ይመለከቱት ነበር፡፡ ይህም አጋጣሚ አይሁድ ራሳቸው የሚቃወሙት አዲስ ሃይማኖት መሆኑን እስኪያረጋግጡ ድረስ የሮማውያንን ተቃውሞ ለመቀነስ ረድቶ ነበር፡፡

## ክርስትና በሮም

- በኔሮን ቄሳር ዘመን ክርስቲያኖች በቁጥር በዝተው በሮም ይኖሩ ነበር፡፡ "እምነታችሁ በዓለም ሁሉ ስለ ተሰማች አስቀድሜ ስለ ሁላችሁ አምላኬን በኢየሱስ ክርስቶስ አመሰግናለሁ::" *ሮሜ 1፡8፣ ሮሜ 16፡5-15፡፡*
- ክርስቲያኖች ከሁሉ ይልቅ በሁለቱ የሮም ቄሳሮች በኔሮንና በድምጥያኖስ ዘመን ከፍተኛ መከራዎችን ተቀብለዋል፡፡

## *የኔሮን ቄሳር ዘመነ መንግሥት መከራ*

- በጁላይ 18፡ 64 ዓ.ም. ለስድስት ቀናት የቆየ የእሳት አደጋ በሮም ከተማ ላይ ደርሶ ከፍ ያለ ጉዳት አድርሶ ነበር፡፡
- የእሳቱ አደጋ መንሥኤም ራሱ ንጉሡ ነበር፡፡ ይህን ያደረገውም በራሱ ስም ሌላ ታላቅ ከተማ ለመመሥረት አስቦ ነበር፡፡
- እሳቱ ሲነሳም መንስኤው ክርስቲያኖች ናቸው በማለት ይህንኑ ምክንያት በርካታ ክርስቲያኖችን በግፍ ለመጨፍጨፍ ተጠቀመበት፡፡

## *የድምጥያኖስ ቄሳር ዘመነ መንግሥት መከራ*

- ድምጥያኖስ ራሱን "እግዚአብሔርና ጌታ" ማንኛውንም ክርስቲያን ደግሞ ጠላት አድርጎ ይቆጥር ነበር፡፡
- የገዛ ዘመዶቹን ጨምሮ በርካታ ክርስቲያኖችን ገድሎ ነበር፡፡
- ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስን ካሰረው በኋላ በፍጥሞ ደሴት ያጋዘው ድምጥያኖስ ነበር፡፡

## *ምን ተማርን?*

- ሐዋርያትን የረዳቸው ጌታ ዛሬም እኛን የሚረዳን መሆኑን በመረዳት እርዳታውን በጸሎት መጠየቅ እንደሚገባን፡፡
- መንፈሳዊ አገልግሎት ዛሬም ቢሆን ከባድ አለመሆኑን፣ ዛሬ በመጀመር ጥቂት ጥረት በማድረግ ሌሎች የክርስቶስን ብርሃንን በማየት እንደ እኛ እንዲደሰቱ ፈጽመን ቀጥ ያለ አቋም ያለን ሆነን መቅረብን
- ክርስቲያኖች ላልሆኑት ወደ ቤተ ክርስቲያናችን አምነው ይመለሱ ዘንድ ከቤ/ክ በር በፊት ልባችንን በፍቅር እንከፍትላቸው ዘንድ እንደሚገባን፡፡

# ቤተ ክርስቲያን - በዘመነ ሐዋርያት

## *ሥርዓተ አምልኮ በሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን*

### (ሀ) መግቢያ

- ቤተክርስቲያን በሐዋርያት ትምህርትና ሐሳብ የእግዚአብሔር ቤት ናት፡፡ *"ነገር ግን ብዘገይ በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት መኖር እንዴት እንደሚገባ ታውቅ ዘንድ እጽፍልሃለሁ፤ቤቱም የእውነት ዓምድና መሠረት የሕያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ነው፡፡" ቀዳ ጢሞ. 3፡15 ፡፡* ቤተክርስቲያን የክርስቶስ ሙሽራ ናት፡፡
- በቤተክርስቲያን በሚፈጽሙ ምሥጢራት በረከትና ጸጋ እናገኛለን፤በዘመነ ሐዋርያት የነበረችው ቤተክርስቲያንም ለምሥጢራት ጥቅም ትኩረት ነበራችው፡፡*በሐዋርያት ሥራ ምዕ. 9 እና 10* የተጠቀሰውን የሳውልንና የቆርነሌዎስን ጥምቀት ታሪክ አንብቡ፡፡

### (ለ) የጌታ እለት - እሁድ

- ጌታችን ከሙታን ተለይቶ የተነሳባት ስለሆነች የጌታ ቀን ትባላለች፡፡እሁድ አይሁድ የሚያከብርዋትን ቅዳሜ ተክታለች፡፡
- በመጽሐፍ ቅዱስ እሁድ ክርስቲያኖች ተሰባስበው ቅዱስ ቁርባን የሚቀበሉባት መሆኑ ተገልጾዋል፡፡
- "ከስምንት ቀን በኋላም ደቀ መዛሙርቴ ደግመው በውሰጥ የነበሩ፤ቶማስም ከእነርሱ ጋር ነበረ፡፡ ደጆች ተዘግተው ሳሉ ኢየሱስ መጣ፣በመካከላቸውም ቆሞ፡-ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው፡፡" *ዮሐ 20፡26* "ከሳምንቱም በመጀመሪያ ቀን እንጀራ ለመቁረስ ተሰብስበን ሳለን፣ጳውሎስ በነገው ሊሄድ ስላሰበ ከእነርሱ ጋር ይነጋገር ነበር፣እስከመንፈቀ ሌሊትም ነገሩን አስረዘመ፡፡"*የሐ.ሥራ 20፡7* "እኔ ስመጣ ይህ የገንዘብ ማዋጣት ያን ጊዜ እንዳይሆን፣ ከእናንተ እያንዳንዱ በየሳምንቱ በፊተኛው ቀን እንደ ቀናው መጠን እያስቀረ በቤቱ ያስቀምጥ፡፡" *ቀዳ ቆሮ16፡2፡፡*

### (ሐ) ለአምልኮ መሠባሰብ

*ቦታዎች*

- የሥርዓተ አምልኮ መሠባሰቢያቸው በቤቶች ነበር፡፡ለምሳሌ በበዓለ ሀምሳ በተሰባሰቡበት በማርቆስ እናት በማርያም ቤት ነበሩ፡፡ *ሥራ 2፡1-ፍጻሜ፣ ሥራ 12፡12፡፡*

# ቤተ ክርስቲያን - በዘመነ ሐዋርያት

## ሥርዓቱ

- በቅዱስ ቁርባን ጊዜ ወንጌል በማንበብ ይጀመራል፣ የነቢያት ትንቢት ይነበባል፣ ስብከት ከተሠጠ በኋላ ጸሎት ይደረጋል። ጸሎቱም ስለ ቤተክርስቲያን ጉዳዮች፣ ስለ ሠላም እና የምሥጢራት አፈጻጸም ጸሎት ናቸው። *ሥራ 1:14፣ 3:1፣6:4፣ 12:5፣ ቆላ 1:9፣ ቀዳ ጢሞ 4:5፣ ራእ 5:8፣ 8:4-5።*

## አጋፔ "የምዕመናን ስብስብ-አንድነት"

- አጋፔ በሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን የታወቀ ነው።ክርስቲያኖች በአንድነት ተሰባስበው መዝሙር የሚዘምሩበት የሚማሩበትና የሚመገቡበት ነበር።በመጀመሪያ አጋፔ ከቅዱስ ቁርባን ጋር የሚፈጽሙ ነበሩ። በኋላ ግን ሁለቱን ሙሉ በሙሉ ለይተዋል። *ቀዳ ቆሮ 11:1-…።*

## ጸሎት

- ወንዶችና ሴቶች ለሁለት ተከፍለው ይጸልዩ ነበር። ጸሎቱም የጌታችንን ጸሎት ነበር።"እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ ፡- በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ ስምህ ይቀደስ መንግስትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን ከክፉም አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን መንግሥት ያንተ ናትና ኃይልም ክብርም ለዘለዓለሙ አሜን።" *ማቴ. 6:9-13* መዝሙረ ዳዊትም የጸሎቱ ክፍል ነበር። "እንግዲህ፣ወንድሞች ሆይ፣ምንድር ነው? በምትሰበሰቡበት ጊዜ ለእያንዳንዱ መዝሙር አለው፣ትምህርት አለው፣መግለጥ አለው፣በልሳን መናገር አለው፣መተርጎም አለው፣ሁሉ ለማነጽ ይሁን።" *ቀዳ ቆሮ. 14 :26*
  እንዲሁም "ይህ ማባከን ነውና በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ" *ኤ.ፌ. 5:19።*

## መዝሙራት

- በዘመነ ሐዋርያትም መዝሙር ይዘመር ነበር "በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ፤ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ።" *ኤፌ. 5:19* እና "የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ። በጥበብ ሁሉ እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገሥጹ። በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ።" *ቆላ. 3:16።*

## የመስቀል ምልክት

- የክርስቶስ መስቀል ከመጀመሪያ ጀምሮ ለክርስቲያኖች የክብርና የቅድስና ምልክት ነበር። በደረታቸው እና በክንዳቸው ይነቀሱትም ነበር።የመስቀል ምልክት ያደርጉ የነበሩትም የመስቀልን ኃይል ለማግኘት፣ ዲያብሎስን ለማሸነፍ እና በመስቀል የተገለጠውን የጌታችንን ፍቅር ለማስታወስም ነበር። "የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፣ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና;; " *ቀዳ ቆሮ. 1:18፣ ገላ 6:14።*

# ቤተ ክርስቲያን - በዘመነ ሐዋርያት

***ጾም***

- ስለሰባቱ አጽዋማት ከዚህ በፊት በተሰጠን ትምህርት መሠረት ከመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጀምሮ የሚፈጸም ነበር። ***ሥራ 13፡2-3።***

***የሙታን ጸሎት***

- በዘመነ ሐዋርያት የነበረችው ቤተክርስቲያን ለሙታን ትጸልይ ነበር። ቤተክርስቲያን ለሙታን በሚደረግ ጸሎት ሙታንና የሚጸልዩት ሕያዋን እንደሚጠቀሙበት ታምናለች።ቅዱስ ዮሐንስ ይሄንን ሲያጸና "ማንም ወንድሙን ሞት የማይገባውን ኃጢአት ሲያደርግ ቢያየው ይለምን፣ሞትም የማይገባውን ኃጢአት ላደረጉት ሕይወት ይሰጥለታል። ሞት የሚገባው ኃጢአት አለ፤ስለዚያ እንዲጠይቅ አልልም።" ***ቀዳ ዮሐ. 5፡16*** "እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነትም ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር፣ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ። ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው።" ***ቀዳ ጢሞ. 2፡1-3*** "በዚያን ቀን ከጌታ ምሕረትን እንዲያገኝ ጌታ ይስጠው፤በኤፌሶንም እንዴት እንዳገለገለኝ አንተ በደኅና ታውቃለህ።" ***ካል ጢሞ. 1፡18።***
- ይህም ማለት በሃይማኖት ኖረው ያላወቁት ኃጢአት (ስህተት) ለሥሩ የሚደረግ ጸሎት ጸሎተ ፍትሐት ነው።

***ምን ተማርን?***

(1) በሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን እንኑር።በዓለም ብዙ የሐሰት ሃይሞኖቶች እንሠማለን። በነዚህ የሐሰት ትምህርቶች ልንሳብባቸው ግን አይገባም። ቤተክርስቲያናችን በታሪክና በመንፈስ ከዘመነ ሐዋርያት ጋር አንድ ናት።

(2) ሥርዓተ አምልኮታችንን መቀየር ምን ያመጣል? ሥርዓተ አምልኮታችንን ከቀየርን ሐዋርያዊ ሥርዓተ አምልኮትን አናጸናም። በመለወጥ የሚገኝ ትርፍም የለም።ቤተክርስቲያንና ሰዎችን ከሙጉዳት በስተቀር ሌሎች በክርስትና ስም የሚንቀሳቀሱ ክፍልፋዮች በዚህ የለውጥ እንቅስቃሴ በአስከፊ ሁኔታ ይሄን በረከት አጥተዋል። ለዚህም ነው የጭፈራ ቤት ትዕይንትን አምልኮ የሚሉት። ***"ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት ዛሬ ለዘላለምም ያው ነው። ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትውሰዱ። ዕብ. 13፡8-9።***

# ቤተ ክርስቲያን - በዘመነ ሐዋርያት

***ምን ተማርን?***

(1) **በሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን እንኑር፡፡በዓለም ብዙ የሐሰት ሃይሞኖቶች እንሠማለን፡፡ በነዚህ የሐሰት ትምህርቶች ልንሳብባቸው ግን አይገባም፡፡ ቤተክርስቲያናችን በታሪክና በመንፈስ ከዘመነ ሐዋርያት ጋር አንድ ናት፡፡**

(2) *ሥርዓተ አምልኮታችንን መቀየር ምን ያመጣል? ሥርዓተ አምልኮታችንን ከቀየርን ሐዋርያዊ ሥርዓተ አምልኮትን አናጸናም፡፡ በመለወጥ የሚገኝ ትርፍም የለም፡፡ቤተክርስቲያንና ሰዎችን ከሙጉዳት በስተቀር ሌሎች በክርስትና ስም የሚንቀሳቀሱ ክፍልፋዮች በዚህ የለውጥ እንቅስቃሴ በአስከፊ ሁኔታ ይሄን በረከት አጥተዋል፡፡ ለዚህም ነው የጭፈራ ቤት ትዕይንትን አምልኮ የሚሉት፡፡* ***"ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት ዛሬ ለዘላለምም ያው ነው፡፡ ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትውሰዱ፡፡*** *ዕብ. 13፡8-9፡፡*

# ይቀጥላል…

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org